# የፀማይ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ይድነቃቸው ከበደ
መስፍን እሸቱ
የትናየት ደሳለኝ

የጥናቱ አጠቃላይ ሂደት እንደሚጠቁመው የፀማይ ብሔረሰብ ባህላዊ የሕግና የፍትሕ ሥርዓታቸውን በመጠቀም በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ይፈታሉ፤ ግጭቶች ከመከሰታቸው በፊት አስቀድመው ይከላከላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ይሁንታዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

- የፀማይ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቺያ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት እና ተቀባይነት ከግምት በማስገባት የባህላዊ ህጎችንና የባህላዊ ተቋማትን አሰራር በተመለከተ ዝርዝር ሕግ በሕግ አውጪው አለመውጣቱ በአፈፃጸም ረገድ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ በመሆኑም የሕግ አውጪው አካል ዝርዝር ሕግን በማውጣት ይህን ችግር ሊፈታው ይገባል፡፡
- ከዚህ በፊትም ሆነ ወደ ፊት በባህላዊ ሕግ ዙሪያ ለተደረጉት እና ለሚደረጉት ጥናቶች የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተለይም በዚህ በኩል የትኞቹ የባህላዊ ሕጎች እና ቷቋማት ናቸው ጠቃሚዎቹ? ሕገ መንግስቱ ካስቀመጣቸው መሰረታዊ መርሆዎች ጋር ተጣጥመው መሄድ የሚችሉት እንዴት ነው? ባህላዊው ሕግና መደበኛው የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓት እንዴት ሊመጋገቡ ይችላሉ? ወዘተ… የሚሉትን በስፋት መርምሮ ጠቃሚ የሚባሉትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ግጭቶችን አስቀድሞ የመከላከል እና ሲከሰቱም በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሚሆነው የህዝብ ተሳትፎ ሲኖር ነው፡፡ የማህበረሰቡ ተሣትፎ መኖር የፀማይ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት አይነተኛ መገለጫ እንደመሆኑ በየደረጃው ያሉ የፖለቲካው ሥርዓትና የመደበኛው የፍትሕ አካላት ግጭቶችን እንዴት መከላከል እና መቆጣጠር ብሎም መፍታት እንደሚቻል በግጭት ፈቺነት የሚሳተፉት የሀገር ሽማግሌዎች ምክር የሚያገኙበትን አደረጃጀት፣ መዋቅር እና አሰራር መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

- እያንዳንዱ ግጭት የራሱ ባህርይና መንስዔ እንዳለው በመረዳት ከግጭቱ ዓይነትና ከህዝቡ ባህል አንፃር እየታየ ከአካባቢው ባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማት ጋር በህብረት በመስራት ግጭቶችን የመፍታት ልምድ ይበልጥ የሚዳብርበት ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- የፀማይ ብሔረሰብ ባህላዊ የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓት አሁንም አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን እየተዳከመ በመሆኑ መንግሥትና የሚመለከተው አካል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡